# የብረታ ብረት ማቅለጫና ማምረቻ ፋብሪካው የሙከራ ምርት ጀመረ

መቀሌ, ግንቦት 14 ቀን 2001 (መቀሌ) - መቀሌ ከተማ ውስጥ በ96 ሚሊዩን ብር በመገንባት ላይ ያለው የአበሲኒያ ብረታ ብረት ማቅለጫና ማምረቻ ፋብሪካ የሙከራ ምርት መጀመሩን የፋብሪካው ባለቤትና ዋና ድሬክተር አስታወቁ፡፡

የፋብሪካው ባለቤትና ዋና ድሬክተር ሚስተር ጃቲን ፔተል ከትናንት በስተያ እንደገለጡት በ56 ሺህ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ ያረፈው ይኸው ፋብሪካ በአመት 16 ሜትሪክ ቶን ብረታ ብረት የማምረት አቅም አለው፡፡

ፋብሪካው የሙከራ ምርት የጀመረው የአንደኛው ምእራፍ ግንባታ በመጠናቀቁ እንደሆነ ገልጠው፣ ሁለተኛውን ምእራፍ ለመገንባት እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ፋብሪካ በመጀመሪያው ምእራፍ ለ600 ሰራተኞች የስራ እድል መፍጠሩንና የሁለተኛው ምእራፍ ሲጠናቀቅ ደግሞ የሰራተኞቹ ቁጥር ወደ 1 ሺህ 200 ከፍ እንደሚል ገልጠዋል፡፡

ፋብሪካው የወዳደቁ ብረታ ብረትና ቆርቆሮ በማቅለጥ ለተለያየ ግንባታ የሚያገለግሉ ብረታ ብረት እንደሚያመርት አመልክተዋል፡፡

ፋብሪካው ለበር፡ ለመስኮት፣ ለአርማታ የሚውሉ ብረታ ብረት ፣ ምስማርና ሌሎችን በማምረት ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የትግራይ ክልል ርእስ መስተዳድር አቶ ጸጋይ በርሄ ከትናንት በስተያ ፋብሪካውን በጎበኙበት ወቅት እንደተናገሩት ፋብሪካው ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ብረታ ብረት በማምረትና የስራ እድል ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል ፡፡

ፋብሪካው የጀመረው ተግባር ተጠናክሮ እንዲቀጥል የክልሉ መስተዳድር አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግም አረጋግጠዋል፡፡

ሪፖ/ኤዲ/ 12.00-12.20 ጠሰድ=0.20 ጥ/ከፍ/